በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 4!!!

## <u>ፕሮቴስታንቲዝም - 1</u>

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

*<u>ቦታ፡-</u>* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

የካቲት ፲ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.


# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## መግቢያ

- ፕሮቴስታንቲዝም እ.አ.አ በ1517 ዓ.ም. በአውሮፓ ከተደረገው የፕሮቴስታንት (የተቃውሞ) ተሐድሶ የተወለደ እንቅስቃሴ ነው።
- ይህም የተቃውሞ እንቅስቃሴ በወቅቱ በትምህርተ ሃይማኖት አስተምህሮዋ በርካታ ሕጸጾች የተገኙባት፣ የመንፈስቅዱስ ስጦታዎችን በገንዘብ በመለዋወጥ ሥራ ተጠምዳ (ሲሞናዊነት) የነበረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያነጣጠረና ከውስጥዋም የፈለቀ ነበር። *የሐዋ 8፡18-19።*
- ይህ በሮም ላይ የተቀጣጠለው የተቃውሞ እንቅስቃሴ የተጀመረው እ.አ.አ በ1517 ዓ.ም. ማርቲን ሉተርና፤ አውግስጢዊው መነኩሴና የዊተንበርግ ፕሮፌሰር በኃጢአት ሥርየት ጉዳይ በካቶሊኩ ፖፕ ይፈጸማል ስላሉት ሽያጭ ወይም ፖፑ ኃጢአትን በገንዘብ የማስተስረይ ድርጊታቸው በድጋሚ ክርክር እንዲደረግበት ጥሪ ባደረጉበት ወቅት ነው።
- የካቶሊክ ቤ/ክ በወቅቱ ኃጢአተኛ ሰው ንስሐ ገብቶ ከበደሉ እንዲነጻ ብሎም ወደ ገነት እንዲገባ ከፈለገ ገንዘብ የመክፈል ግዴታ ጥላበት ነበር።
- ሉተርም ይህንኑ በመቃወም በዊተንበርግ ካስል ቸርች በር ላይ ለዩኒቨርስቲ ማስታወቂያ መለጠፊያነት ያገለግል በነበረው ቦታ 95 የተቃውሞ ቴሲሶችን ጽፎ ለጠፈ።

# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## የማርቲን ሉተር 95 የተቃውሞ ቴሲሶች



AMORE ET STVDIO ELVCIDANDAE ueritatis hæc subscripta disputabunt Vuittenbergæ, Præsidēte R. P. Martino Luther, Artiū & S. Theologiæ Magistro, eiusdemq; ibidem lectore Ordinario. Quare petit ut qui non possunt uerbis præsentes nobiscum disceptare, agant id literis absentes. In nomine domini nostri Iesu Christi. Amen.

i Dominus & Magister noster Iesus Christus, dicendo pœnitentiā agite &c. omnem uitam fidelium, pœnitentiam esse uoluit.

ij Quod uerbū pœnitentia de pœnitentia sacramentali (.i. confessionis & satisfactionis quæ sacerdotum ministerio celebratur) non potest intelligi.

iij Non tamen solū intēdit interiorē; immo interior nulla est, nisi foris operetur uarias carnis mortificationes.

iiij Manet itaq; pœna donec manet odium sui (.i. pœnitentia uera intus) scilicet usq; ad introitum regni cælorum.

v Papa non uult nec potest, ullas pœnas remittere; præter eas, quas arbitrio uel suo uel canonum imposuit.

vj Papa nō potest remittere ullam culpā, nisi declarādo & approbando remissam a deo. Aut certe remittēdo casus reseruatos sibi, quibus contēptis culpa prorsus remaneret.

vij Nulli prorsus remittit deus culpam, quin simul eum subijciat humiliatum in omnibus sacerdoti suo uicario.

viij Canones pœnitenciales solū uiuentibus sunt impositi; nihilq; morituris, secundū eosdem debet imponi.

ix Inde bene nobis facit spiritussanctus in Papa; excipiēdo in suis decretis semper articulum mortis & necessitatis.

x Indocte & male faciūt sacerdotes ij, qui morituris pœnitētias canonicas in purgatorium reseruant.

xj Zizania illa de mutanda pœna Canonica in pœnā purgatorij, uidentur certe dormientibus Episcopis seminata.

xij Olim pœnæ canonicæ nō post, sed ante absolutionem imponebantur, tanq; tentamenta uerae contritionis.

DISPVTATIO DE VIRTVTE INDVLGEN.

xiij Morituri, per mortem omnia soluunt, & legibus canonū mortui iam sunt, habentes iure earū relaxationem.

xiiij Imperfecta sanitas seu charitas morituri, necessario secum fert magnū timorem, tātoq; maiorē, quāto minor fuerit ipsa.

xv Hic timor & horror, satis est, se solo (ut alia taceam) facere pœnam purgatorij, cum sit proximus desperationis horrori.

xvj Videntur, infernus, purgatorium, cœlum differre; sicut desperatio, prope desperatio, securitas differunt.

xvij Necessarium uidetur animabus in purgatorio sicut minui horrorem, ita augeri charitatem.

xviij Nec probatū uidetur ullis, aut rationibus, aut scripturis, q; sint extra statum meriti seu augendæ charitatis.

xix Nec hoc probatū esse uidetur, q; sint de sua beatitudine certæ & securæ, saltem oēs, licet nos certissimi simus.

xx Igit̄ Papa per remissionē plenariā omniū pœnarū, non simpliciter omniū intelligit, sed a seipo tm̄modo impositarū.

xxj Errant itaq; indulgentiarū prædicatores ij, qui dicunt per Papæ indulgentias, hominē ab omni pœna solui & saluari.

xxij Quin nullam remittit animabus in purgatorio, quā in hac uita debuissent secundum Canones soluere.

xxiij Si remissio ulla omniū omnino pœnarū pōt alicui dari; certū est eam nō nisi perfectissimis .i. paucissimis dari.

xxiiij Falli ob id necesse est, maiorem partē populi; per indifferentē illam & magnificam pœnæ solutæ promissionem.

xxv Qualē potestatē habet Papa ī purgatoriū gn̄aliter talē habet qlibet Episcopus & curat⁹ in sua diocesi, & parochia sp̄aliter.

i Optime facit Papa, q; nō potestate clauis (quā nullam habet) sed per modum suffragij, dat animabus remissionem.

ij Hominē prædicant, qui statim, ut iactus nūmus in cistam tinnierit, euolare dicunt animam.

iij Certū est nūmo in cistam tinniente, augeri quæstum & auariciam posse: suffragiū aūt ecclesiæ est in arbitrio dei solius.

iiij Quis scit si omnes animæ in purgatorio uelint redimi, sicut de sancto Seuerino & paschali factum narratur?

v Nullus securus est de ueritate suæ contritionis; multo minus

a ij

# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## መግቢያ

- ሉተር ካቶሊካዊ መነኩሴ በነበረበት ዘመን የሮም ጳጳሳትን ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች የተመረጡ የተለዩ አድርጎ ለማሽሞንሞን ቢሞክርም ክህነታቸውና የሚፈጽሟቸው ምስጢራትም ከሐዋርያት የተወረሰ መሆኑን በተመለከተ ግን ተቀባይነት የሌለውና የማይቀበለውም መሆኑን  አስምሮበታል፡፡
- ሉተር በርካታዎቹን የካቶሊክ ምስጢራት፣ ንስሐን በገንዘብ መፈጸምንና የእምነትን ያህል የሥራን አስፈላጊነት ባይቀባላቸውም ጥምቀትና ቁርባን ግን ያስፈልጋሉ ብሎ ነበር፡፡
- ከመጀመሪያው የተቃውሞ እንቅስቃሴ፣ ከሉተር የካቶሊክ ቤ/ክ መለየትና ፖፑም የተሐድሶን እንቅስቃሴ ካወገዙ በኋላ የጆን ካልቪን ጽሑፎችና ሥራዎች በስዊትዘርላንድ፣ ስኮትላንድ፣ ሃንጋሪ፣ ጀርመንና በሌሎችም ሥፍራዎች በነበሩ የፕሮቴስታንት ቡድኖች መካከል ልል የሆነ መስማማትን ፈጥሮላቸው ነበር፡፡
- ይህን ተከትሎም ፕሮቴስታንቲዝምም በፍጥነት በስዊትዘርላንድ፣በስካንዲኔቪያ፣ በእንግሊዝ፣ ስኮትላንድ፣ ኔዘርላንድና ፈረንሳይ ተዛመተ፡፡
- ይህም የተሐድሶ እንቅስቃሴ ለ30 ዓመታት የዘለቀ የሃይማኖት ጦርነት ቀስቅሶ ነበር፡፡

# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## መግቢያ

- እ.አ.አ. ከ1618 ዓ.ም. እስከ 1648 ዓ.ም. ስፔንን፣ ኦስትሪያንና የኔዘርላንድ ስፓኒሾች፣ በርካታ ጀርመኖችና ጣሊያኖችን የመራው ካቶሊካዊው ሃብስበርግስ በዴንማርክና በስዊድን ይደገፉ ከነበሩት ፕሮቴስታንታዊ የጀርመን እቴጌዎች ጋር ጦርነት አካሂዷል፡፡
- ይህም የተሐድሶ እንቅስቃሴ ካቶሊካዊት ፈረንሳይ በቅድሚያ በድብቅ በማስከተልምሀበስበርግስን በመቃወም ከፕሮቴስታንቶች ጋር በመወገን በጦርነት ስትሳተፍ ፍጻሜ አግኝቷል፡፡
- ይህም ከሉተር በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በአውሮፓ ምድር ፖለቲካዊና አገራዊ ጉዳይ ከሃይማኖታዊ ጉዳይ በላይ የተፈለገ ሆኖ ሃይማኖት የፖለቲካ መሳሪያ ሆኖ ሲያገለግል ታይቷል፡፡

# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## *በፕሮቴስታንቲዝም ተሐድሶ የተፈጠሩ አብያተ ክርስቲያናት*

- አንግሊካኒዝም
- አናባፕቲዝም
- ካልቪኒዝም
- ሉተራኒዝም
- ዝዊንግሊያኒዝም

## *ከፕሮቴስታንቲዝም ተሐድሶ በኋላ የተፈጠሩ አብያተ ክርስቲያናት*

- ባፕቲስቶች
- ፒየቲዝም
- ጰንጤቆስጣሊዝም
- ፑሪታኒዝም
- ዛሬ ከ33,000 በላይ የፕሮቴስታንት ቡድኖች በዓለማችን ይገኛሉ።

# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## *የፕሮቴስታንት የእምነት ፍልስፍና መሠረቶች*

- በወቅቱ የሮማ ካቶሊክን በመቃወም የፕሮቴስታን ተሐድሶ እንቅስቃሴ አራማጆች ያነገቡአቸው አምስት መፈክሮች ነበሩ። እነዚህ በላቲን ቋንቋ ሶላስ ተብለው ይታወቃሉ። ሶላ ማለትም ‹‹ብቻ›› ወይም ‹‹ብቸኛ›› ማለት ሲሆን እንደ እንቅስቃሴው አራማጆች ለመዳን የሚያስፈልጉት አምስቱ ሶላዎች ናቸው ወደሚል ድምዳሜ የደረሱባቸው ናቸው።

- እነዚህም አምስቱ ሶላዎች፡-
    1. ሶለስ ኪርስተስ - ክርስቶስ ብቻ
    2. ሶላ ስክሪፕቱራ - የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል ብቻ
    3. ሶላ ፊዴ - እምነት ብቻ
    4. ሶላ ግራሺያ - ጸጋ ብቻ
    5. ሶሊ ዴ ግሎሪያ - ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ የሚሉ ናቸው።

# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## ሶለስ ኪርስተስ - ክርስቶስ ብቻ

- ፕሮቴስታንቶች ፖፕ በምድር ያለች ቤ/ክ ብቸኛ የክርስቶስ ተወካይ የሚለውን ዶግማ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ ብቸኛው ‹‹አማላጅ›› ክርስቶስ ነው የሚለውን ትምህርት የካደ ነው በማለት ራሳቸው ስተው ካቶሊኮችንም ይቃወሙበታል፡፡ ‹‹እርሱ ግን እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው፡፡›› *ቀዳ ዮሐ 5፡20፡፡*

## ሶላ ስክሪፕቱራ - የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል ብቻ

- ፕሮቴስታንቶች የእውነተኛይቱ አንዲት፣ ዓለም አቀፋዊት፣ ሐዋርያዊትና ንጽሕት ቤ/ክ መሠረተ እምነት ከታሪክና ከመሠረተ እምነት ጋር እየተቀላቀለ አደናቃፊ ሚና ይጫወታል ይላሉ፡፡
- ይልቁንም ፕሮቴስታንቶች በቃል ሲተላለፉ የኖሩ እውነተኛ ትውፊቶችንና የአባቶችን አስተምህሮ ሥልጣን የሌላቸው ተራ ስብእና ያላቸው ሰዎች ንግግር አድርገው ይቆጥራሉ፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ግን ‹‹ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል፡፡የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡›› *ካል ጢሞ 3፡15-17፣ ካል ተሰ 2፡12፡፡* ይላቸዋል፡፡

# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## ሶላ ፊዴ - እምነት ብቻ

- ፕሮቴስታንቶች *በኤፌ 2፡8-9* እንደ ተጠቀሰው በክርስቶስ ያለ እምነት ብቻ በቂ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ነገር ግን እውነተኛይቱ ሐዋርያዊት ቤ/ክ ግን *በያዕ 2፡20* እንደተጠቀሰው ‹‹ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ መሆኑን››፣ *ያዕ 2፡24* ደግሞ ‹‹ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ፡፡›› እንደተባለ ለመዳን የሚያስፈልጉት ሁሉ መጓደል እንደሌለባቸው አምና ለማሳመን ታስተምራለች፡፡

## ሶላ ግራሺያ - ጸጋ ብቻ

- ፕሮቴስታንቶች መዳን በክርስቶስ የተሰጠ ስጦታ ስለሆነ ሥራ አያስፈልገውም ማንም ቢሆን ‹‹እስካመነ›› ይድናል በማለት *ማቴ 7፡22-23፡፡* ‹‹በዚያ ቀን ብዙዎች፡፡ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል፡፡የዚያን ጊዜም፡፡ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ፡፡›› በማለት በክርስትና ሃይማኖት ኑሮአችን ጥንቃቄ እንዲከበን ያስተማረን የጌታችንን ትምህርት ያቃልላሉ፡፡

# ፕሮቴስታንቲዝም - 1

## *ሶሊ ዴ ግሎሪያ - ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ*

- ፕሮቴስታንቶች/ተሐድሶዎች በቤተ ክርስቲያን ቀኖና የተመረጡትን ቅዱሳን ሳይቀር ክብር እንደማይገባቸው ያምናሉ፡፡ በዚህም *ቀዳ ቆሮ 15፡41* ‹‹የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው፤ በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያልና፡፡››፣ ‹‹አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው፡፡›› *ሮሜ 8፡30፡፡*
- የተባለውን የአምላካዊ ክብርንና አምላካችን እግዚአብሔር ወዳጆቹን እንድናከብር የፈቀበደትን ለይቶ ባለመረዳት ይቀላቅላሉ፡፡ እነዚህም *በኤፌ 5፡27* ‹‹እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ፡፡›› ያለውን የክርስቶስን ትምህርት የሚያስተሃቅሩ ሲሆኑ *በመዝ 30(31)፡18* ‹‹በድፍረትና በትዕቢት በመናቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ፡፡›› ብሎ የተነገረባቸው ናቸው፡፡
- *ቀዳ ጴጥ 1፡8-9* ‹‹እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁንም ምንም ባታዩት በእርሱ አምናችሁ፥ የእምነታችሁን ፍፃሜ እርሱም የነፍሳችሁን መዳን እየተቀበላችሁ፥ በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ይላችኋል፡፡›› እንደተባልን ያከበራቸውን እያከበርን ወደክብር ከፍ እንል ዘንድ እንደሚገባን እናስተውል ዘንድ ይገባል፡፡

# ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org